# The preconditions of La ilaha ila Allah

# የላ ኢላሃ ኢለሏህ ቅድመ ሁኔታዎች




በወጣቱ ተልዕኮ(አህመድ የሱፍ)

## Presented by: Youth-Mission Online Amharic Islamic Books Publishing.

# The preconditions of La ilaha ila Allah

# የላ ኢላሃ ኢለሏህ ቅድመ ሁኔታዎች


## በጀማል አዲን ዛራቦዞ

## ትርጉምና ቅንብር በአህመድ የሱፍ



**All right reserved**

**© የወጣቱ ተልዕኮ**



**የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008**

**ሰሜን ወሎ ወልዲያ**



**ahmedyesuf29@gmail.com**

**+251927790323**



**http://youth-mission.mobie.in**


የላኢላሃ ኢለሏህ የምስክርነት ቃል የጀነት ቁልፍ ነው። ታዲያ ይህ የምስክርነት ቃል መሉ ይሆን ዘንድ ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። የቁርአን አናቅፅቶችን እና የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ብናጠና የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታዎች በቁጥር ስምንት ወይም ዘጠኝ እንደሆኑ እንረዳለን። ሆኖም ሁላችነም እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በህይወታችን የራሳችነን የእምነት ምስክርነት ያሟላን መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ነገሮች ከመበላሸታቸውና አቅጣጫ ስተው ከመሄዳቸው በፊት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚሟላት የቻልነውን ሁሉ ማድረግ አለብን።

# መግቢያ

## በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

እኛ ሙስሊሞች የጀነት ቁልፍ ከሊሙቱ ላኢላሃ ኢለሏህ ከአሏህ ውጭ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ የለም የምትለው የምስክርነት ቃል እንደሆነች እናምናለን። ሆኖም ብዙዎቻችን በዚች የምስክርነት ቃል ተመክተን በላኢላሃ ኢለሏህ እስከመሰከርን ድረስ ምንም ነገር እንደማይነካን እና ምንም ነገር እንደማይደርስብን እናስባለን። ሸሃዳን በቃል ከመሰከርን ብቻ ጀነትን እንደምናገኝም እናስባለን።

ከአሏህ ውጭ በሐቅ የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድ የአሏህ መልዕክተኛና ባሪያ መሆናቸውን እመሰክራለሁ ማለት ብቻውን ለመዳን ወይም ነጃ ለመውጣት በቂ አለመሆኑ አያጠያይቅም። በእርግጥም ሙናፊቆች ብዙ ጊዜ ይሏታል ነገርግን አሏህ ውሸታም እንደሆኑና በጣም ጥልቀት ያለው የጀሃነም እሳት ውስጥ እንደሚኖሩ ነው የገለፀው።

ብዙ ኡለማዎችም ይህ ንግግር ወይም የምስክርነት ቃል የጀነት ቁልፍ ነው ብለዋል። ተዋቂ የሆነው ታቢኢ ወሃብ ቢን ሙናባህ አንዴ የላኢላሃ ኢለሏህ ንግግር የጀነት ቁልፍ አይደለምን? ተብሎ ተጠይቆ። አዎ ነው! ነገርግን እያንዳንዱ ቁልፍ ጥርስ አለው። የተስተካከለ ጥርስ ያለው ቁልፍ ይዛችሁ ከመጣችሁ በሩፉን ይከፍትላችኋል። ነገርግን የተስተካከለ ጥርስ ከሌለው በሩፍ አይከፍትላችሁም ሲል በምሳሌ አስረዳ።

ምን ማለት ነው እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የጀነት በሮች ቁልፍ ጥርሶች ሲሆኑ በዚች የምስክርነት ቃል የሚጠቀምባትን ሰው ከማይጠቀምባት ሰው መለያዎች ናቸው።

የቁርአን አናቅፅቶችን እና የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ብናጠና የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታዎች በቁጥር ስምንት ወይም ዘጠኝ እንደሆኑ እንረዳለን። ሆኖም ሁላችነም እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በህይወታችን እና የራሳችነን የእምነት ምስክርነት ያሟላን መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ነገሮች ከመበላሸታቸውና አቅጣጫ ስተው ከመሄዳቸው በፊት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ለሟሟላት የቻልነውን ሁሉ ማድረግ አለብን።

እነዚህን ቅድመሁኔታዎች ለማስተማር ብቻ ተፈልጎ ሳይሆን እራሳችነን ተመልከተን እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላን መሆኑን እና በአሏህ እዝነት የጀነት በሮች በላኢላሃ ኢለሏህ ቁልፍ ይከፈቱልን ዘንድ ጭምር እንጅ።

## ኢልም: እውቀት

የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ እውቀት ነው። በሸሃዳ ላይ መሰረታዊና ጠቅለል ያለ እውቀት ሊኖረን ይገባል። የሸሃዳ ውድቅ የማድረግና የማረጋገጥ መርህ ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን። አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 47:19})>=**

**فَٱعۡلَمۡ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لِذَنۢبِكَ**

**{19} እነሆ ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን እወቅ። ለስተትህም ምህረትን ጠይቅ።**

በሰኺህ ሙስሊም እንደተመዘገበው

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን አውቆ የሞተ ሰው ጀነት ገባ ብለዋል።

በእርግጥም ሸሃዳ በራሱ ምስክርነት ነው። ታዲያ ለሆነ ነገር ስንመሰክር ስለምንመሰክረው ነገር ምንነት ማወቅ አለብን። እንደው ዝንብለን ተነስተን በግምት የምንመሰክረው ነገር አይደለም። እውቀት በሌለን  ነገር ላይ የምናደርገው ምስክርነትም ሆነ ተግባር ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም። አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 43:86})>=**

**إِلَّا مَن شَهِدَ بِٱلۡحَقِّ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ**

**{86} እነርሱ የሚያውቁ ሆነው በእውነት ከመሰከሩት በስተቀር ምልጃን አይችሉም።**

እናም ይህ ቅድመ ሁኔታ በደንብ ግልፅ የሆነ ይመስለኛል። አንድ ሰው ከአሏህ ውጭ አምላክ የለም፤ አሏህም እየሱስ ነው ቢል ወዲያውኑ ይህ ሸሃዳ ትርጉም እንደማይሰጥ እንነግረዋለን። የባህር አምላክ ብለው ለሳምንት ያህል የሚዘልቅ አመታዊ በአል የሚያከብሩ ሙስሊሞች በሙስሊም ሃገራት ይኖራሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ለቆሌ የሚያርዱ ፣ በመሻኢሆች የሚመጀኑ ፣ የደጋግ ሰዎችን ቀብር የሚያመልኩ ሙስሊሞችስ ይኖራሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? በእርግጥም አሉ! ሁላቸውም እራሳቸውን ሙስሊም ብለውነው የሚጠሩት፤ በቀን ብዙ ጊዜም ሸሃዳ ያደርጋሉ። ይሁን እንጅ ይህ ለቆሌ የሚያርዱት ፣ የሚሳሉት ፣ ቀብር የሚያመልኩት ቀን በቀን የሚያደርጉትን ሸሃዳ ይሽረዋል። ምክኒያቱም ኩፍርና ኢማን አንድ ላይ አብረው አይሄዱምና። ይሁንእንጅ በሃገራችን ኢትዮጲያ የሚደረጉ አብዛሃኛዎቹ የእምነት ወይም የሸሃዳ ተፃራሪዎች የሚፈፀሙት በአላዋቂነት ነው። ይህን ለማወቅ ለአብዛሃኛው የሙስሊም ማህበረሰብ ስለ ሸሃዳና ስለ ቅድመ ሁኔታዎቹ እንዲሁም የአንድን ሰው ኢስላም ስለሚያበላሹ ነገሮች ጥያቄ አንስተን የዳሰሳ ጥናት ብናደርግ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚያውቁት ነገር እንዴለለ እንረዳለን። በእርግጥ አንዳንድ እውቀት ያላቸውም ሰዎች እነዚህን ነገሮች እያወቁ ለክብርና ለጥቅም ብለው የሚፈፅሙ፤ ሰዎችንም ወደነዚህ ነገሮች የሚያመላክቱ አይጠፉም።

ዛሬ ላይ ሴኩላሪዝም ለምን እንደማንቀበል የሚያስቡ ብዙ ሙስሊሞች አሉ። ሴኩላሪዝም ምንም አይነት ችግር እንደሌለው ያስባሉ። እነዚህ ሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ ይስግዳሉ፤ ሸሃዳንም ደጋግመው ይላሉ። አሁንም ከአሏህ ውጭ የሆነን ህግ አውጭ መቀበል ችግር እንደሌለው ያስባሉ። ታዲያ እነዚህ ሰዎች ምን አይነት ሸሃዳ እያደረጉነው ያሉት? የአሏህን ህግ ከመቀበልና በሱ ከመተዳደር ይልቅ የሰውን ልጅ ህግ የበላይ ማድረግ ምን ይሉታል?

ሁላችነም ቢያንስ የእስልምና መሰረቶችን ለመማርና ለማወቅ የቻልነውን ሁሉ ማድረግ ይኖርብናል። እንደዚሁ የሸሃዳን ምንነት እና ስለ ቅድመ ሁኔታዎቹ ምንነት ጠንቅቀን ማወቅ አለብን። ያኔ የአሏህ ፍቃድ ከሆነ ትክክለኛ ሸሃዳ ማድረግ እንችላለን። ለእሷም ምስክር እንድንሆን በታሰበ ጊዜ ሁሌም ለእውነት ምስክር እንሆናለን።

## እርግጠኝነት

ሁለተኛው የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታ እርግጠኝነት ሲሆን የጥርጣሬ ተቃራኒ ወይም ተፃራሪ ነው። በእርግጥ በኢስላም ማንኛውም የጥርጣሬ አይነት ከኩፍር ከክህደት ጋር አቻ ነው። ሸሃዳ ስናደርግ ፍፁም በሆነ መልኩ እውነት እንደሆነ እርግጠኞች መሆን አለብን። ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን ስንመሰክር ቅንጣት ታህል ማቅማማት ፣ ማወላወልና ማመንታት የለብንም። ይች የእምነት ምስክርነት ቃል በምታመለክተው ነገር ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች መሆንና ማመን አለብን።

አሏህ በቁርአኑ አማኞችን የገለፀው በአሏህ ላይ እምነት ያላቸውና ልቦቻቸው የማያወላውል የማይጠራጠሩ እንደሆኑ ነው። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

=<({አል-ቁርአን 49:15})>=

**إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا۟ وَجَٰهَدُوا۟ بِأَمْ**
**وَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلصَّٰدِقُونَ**

**15 ሙእሚኖች(አማኞች) እነዚያ በአሏህና በመልዕክተኛው ያመኑት ከዚያም ያልተጠራጠሩት በሃብታቸውና በነፍሶቻቸውም በአሏህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚያ እነሱ እውነተኞች ናቸው፡፡**

በሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ከአሏህ ውጭ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን እና እኔ የአሏህ መልዕክተኛ መሆኔን ምንም ሳይጠራጠር መስክሮ ከአሏህ ጋር የሚገናኝ ማንም የለም ጀነት የሚገባ በሆን እንጅ ብለዋል፡፡

በእርግጥ አሏህ ሙናፊቆችን የገለፀላቸው ልክ ልቦቻቸው እንደ ሚያመነታ ወይም እንደሚያወላውል ሰዎች ነው፡፡ አሏህ እንዲህ ይላል፡-

=<({አል-ቁርአን 9:45})>=

**إِنَّمَا يَسْتَـْٔذِنُكَ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ وَٱرْتَابَتْ قُلُوبُهُمْ فَ**
**هُمْ فِى رَيْبِهِمْ يَتَرَدَّدُونَ**

**{45} (ከጀሃድ ነፃ ለመሆን) ፈቃድን የሚጠይቁህ እነዚያ በአሏህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑት ልቦቻቸውም የተጠራጠሩት ብቻ ናቸው። እነሱም በጥርጣሬያቸው ውስጥ ይዋልላሉ።**

ብዙ ኡለማዎች የልብ በሽታ ወይም ልብ ላይ ያለች ጥርጣሬ ከስሜት እና ከዝሙት በላይ ለእምነታችን አደገኛ እንደሆነ ገልፀዋል። ምክኒያቱም ዝሙትና ስሜት ምናልባት የሆነ ግዜ ረክተው ሰውየው ስህተት ላይ እንደሆነ አውቆ እራሱን ሊቆጣጠርና ተውበት አድርጎ መጥፎ ስራዎቹን ሊያቆም ይችላል። ነገርግን ጥርጣሬ ያለምንም መድሃኒት ልብ ላይ ሊቆይ ይችላል። ምናልባት ሰውየው ሙሉ በሙሉ ኢስላምን ለቆ እስኪወጣ ድረስ ወይም ደግሞ ልቡ ላይ እውነተኛ ኢማን ሳይኖረው የጥርጣሬ ባህርን እየቀዘፈ ኢስላምን በከፊል እየተገበረ ሊኖር ይችላል።

ታዲያ የጥርጣሬ ትልቁ መድሃኒት እውቀትን መሻት ሲሆን ብዙዎቹም ጥርጣሬዎች የሚወገዱት ጠንካራ ወይም ጠለቅ ባለ የቁርአን እና የሱና እውቀት ነው። በማጥናት እና በመረዳት እርግጠኝነትን ማግኘት እንችላለን። ብዙ ባጠናን እና በተማርን ቁጥር እርግጠኝነታችን የበለጠ እየጠነከረ እየጠነከረ ይሄዳል።

በዚህ ነጥብ ላይ እስኪ አንድ ምሳሌ እንመልከት። አንዳንድ ሰዎች የሐዲስ ስነ-ፅሁፍ የተሰባሰበው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ ከ200 አመታት ብኋላ እንደሆነ በማመን እራሳቸው ጥርጣሬ ላይ ሁነው በሌሎች ላይ ብዙ ሹብሃዋችን ይነዛሉ። ታዲያ በዚህ የጥርጣሬ ባህር ላይ የሚዋኙት እና ጥርጣሬዎችን የሚነዙት ብዙ ጊዜ ኩፋሮች ቢሆኑም ነገርግን በርካታ

ሙስሊሞች በዚህ በሽታ ተለክፈው ይገኛሉ። እንደውም አንዳንዶች በረሱል መልዕክተኝነት እናምናለን እያሉ ቁርአንን ብቻ ተቀብለው የረሱልን ሐዲስ የማይቀበሉ አሉ። ነገርግን ስለ ሐዲስ አመጣጥ ታሪክ እና እንዴት ተጠብቆ እንደኖረ ጊዜ ወስደን ብናጠና ሁሉም በጥርጣሬ ላይ የተመሰረቱ እምነቶችና ክሶች ወይም አቤቱታዎች በምንም ነገር ላይ ያልተመሰረቱ መሰረተ ቢስ አቤቱታዎች እንደሆኑ እንረዳለን። አንዳንዶች ደግሞ ቁርአን የአሏህ ቃል ስለመሆኑ በመጠራጠር የጅብሪል ንግግር ነው ወይም ቁርአን መህሉቅ ነው ይላሉ።

እስኪ በእርግጠኝነት ዙርያ ሌላ አንድ የመጨረሻ ነጥብ እንመልከት። ቀደም ብለን እንደገለፅነው ጥርጣሬ እና አለማዎቅ ለእምነታችን በጣም አደገኛ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ ናቸው። ቀደም ብለን እንደገለፅነውም ጥርጣሬና ማወላወል በኢስላም ከክህደት ጋር አቻ ናቸው። ሆኖም ሁላችነም ከእንደዚህ አይነት ጥርጣሬ ለመራቅ ከጥርጣሬ ምንጭች እራሳችነን ማፅዳት ይኖርብናል። በተለይ እንዲህ አይነት ሹብሃዎችን የሚነዛው ጎደኞችን ከሆነና ጥርጣሬውንም ለማስተባበል ወይም መልስ ለመስጠት እውቀት ከሌለን እራሳችነን ማራቅ ይኖረብናል። ጓደኞችነም በአሏህ ላይ ወይም በሃይማኖቱ ላይ ሁልጊዜ ጥርጣሬዎችን የሚፈጥርብን ከሆነ ከቻልን እንገስፀዋለን ካልቻልን ግን እምነታችነን ለመጠበቅ ከእሱ ሙሉ በሙሉ ልንርቅ ይገባል። በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሙስሊሞች ስለ ኢስላም ኦረንታሊስቶች የሚያስተምሩትን ትምህርቶች ያጠናሉ ይማራሉ። ምክኒያቱም ስለ ኢስላም ጥናት መሰረት የላቸውምና። እውቀት የትም ይሁን የት መፈለጉ ባይከፋም ነገርግን በሳይንስ ስም የሚያስተምሩትን ግድፈቶቻቸውን አሚን ብለው እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ሙስሊሞች ሞባይላቸውን እና ኮንፒተራቸውን ተጠቅመው የተለያዩ ድህረገፃችን በመጎብኘት መረጃዎችን እያነበቡና እየተመለከቱ ፣ ቻት እያደረጉ መረጃዎችን ይሰበስባሉ። ይሁንና ከሚለጠፍት መረጃዎች ጥሩ መረጃዎች ቢኖሩም በርካታ የማይጠቅሙ ጥርጣሬን በሰው ልቦች ላይ የሚረጩ መጥፎ መረጃዎች በማህበራዊ ድህረገፆችና በዜና ድህረገፆች ላይ ይለጠፋሉና እራሳችነን ከዚህ በሽታ ልንጠብቅ ይገባል። እውቀት የሌለው ሰው መሰረተ ቢስ በሆኑ ክርክሮች ወይም ሃሳቦች ሊሸወድ ይችላል። ይልቁንም ትክክለኛ መረጃ የምንሰበስብባቸውን ድህረገፆች ወይም ብሎገሮች ልንለይ ይገባል። ከዚህ በላይ ግን ከትክክለኛ ምንጭ ጥልቅ የኢስላም እውቀት ለመሻት መጣር ይኖርብናል።

አሏህ ከመራን እና ችሮታውን ከለገሰን ብኋላ ጥርጣሬን እና አላዋቂነትን የምናሸንፍበት ትልቁ ሃይል ሃይማኖታችነን መረዳትና ማወቅ ነው። እውቀት በኖረንም ጊዜ ማንኛውም ሰው ለሚነዛው ሹብሃ ልባችን ቦታ አይኖራትም። የአሏህ ፍቃድ ከሆነም አሏህ በሚከተለው አንቀፅ እንደገልፃቸው አይነት ሰዎች እንሆናለን።

**=<({አል-ቁርአን 35:28})>=**

**إِنَّمَا يَخۡشَى ٱللَّهَ مِنۡ عِبَادِهِ ٱلۡعُلَمَٰٓؤُاْ**

**{28} ከባሮቹ መካከል አሏህን ፈሪዎች እውቀት ያላቸው ብቻ ናቸው።**

## መቀበል

ሶስተኛው የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታ መቀበል ነው። ስለ ሸሃዳ እውቀት ካለንና በእሱም እርግጠኛ ከሆን ሸሃዳ በሚያመለክተው ማንኛውም ነገር በምላሳችን እና በቀልባችን መቀበልንም ማስከተል አለብን። ሸሃዳ እውነት እንደሆነ አውቆና እውነት በመሆኑም እርግጠኛ ሆኖ ሸሃዳንና የያዘችውን ነገር አለመቀበል ያ ከሃዲነት ነው። ምናልባት አንዳንዴ አለመቀበል በኩራት ፣ በቅናት ወይም በሌላ ምክኒያት ሊሆን ይችላል። የሆነ ሆኖ ግን ሸሃዳን ያለመቀበል ትክክለኛ ሸሃዳ ሊሆን አይችልም።

ኡለማዎችም ስለዚህ ቅድመሁኔታ ከላይ እንደተገለፀው ጠቅለል ባለመልኩ ተናግረዋል። ነገርግን ጠለቅ እያልን ስንገባ ደግሞ ልንጠነቀቃቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። እውነተኛ አማኞች ሸሃዳ  የምታመለክተውን ማንኛውንም ነገር ይቀበላሉ። ይህ ማለት አማኞች በቁርአን የተገለፀውን እና ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የገለፁትን ነገር ከፊሉን ተቀብሎ ከፊሉን አለመቀበል ሳይሆን በቁርአን እና በሱና የተገለፀውን ማንኛውንም ነገር ያለምንም ማወላወልና ማቅማማት ሙሉ በሙሉ መቀበል ነው።

**=<({አል-ቁርአን 2:85})>=**

**أَفَتُؤۡمِنُونَ بِبَعۡضِ ٱلۡكِتَٰبِ وَتَكۡفُرُونَ بِبَعۡضٖۚ فَمَا جَزَآءُ مَن يَفۡعَلُ ذَٰلِكَ مِنكُمۡ إِلَّا خِزۡيٞ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يُرَدُّونَ إِلَىٰٓ أَشَدِّ ٱلۡعَذَابِ**

**{85} ከመጽሐፉ በከፊሉ አምናችሁ በከፊሉ ትክዳላችሁን? ከእናንተም ይህን የሚሰራ ሰው ምናዳው ምንድነው በዱንያ ህይወት ውርደት ቢሆን እንጅ። በትንሳኤ ቀንም ወደ ብርቱ ቅጣት ይመለሳሉ። አሏህም ከምትሰሩት ስራ ሁሉ ዘንጊ አይደለም።**

ይህ እኛ ሙስሊሞች ልንጠነቀቃቸው ከሚገቡ ነገሮች አንዱ ነው። ምናልባት ከፊሉን እውነታ በመካድ እውነትን ለመቀበል ሙሉ በሙሉ ከመካድ ጋር ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። ነገርግን የእምነት ምስክርነትን ያፈርሳል።

በሚያሳዝን ሁኔታ ዛሬ አንዳንድ ሙስሊሞች ይህን በተለያየ መንገድ ሲያደርጉት ይስተዋላል። ምናልባት ይህ እንደ ክህደት ላይቆጠር ይችላል። ነገርግን በጣም አደገኛ ናቸው። ለምሳሌ አንድ የቁርአን አንቀፅ ላይ የተገለፀውን ካልወደዱት አንቀፁን እንደፈለጉ ይተረጉሙታል። እንዲሁም በሐዲስ የተገለፀውን ነገር ካልወደዱት ሐዲሱ ሰኺህ አይደለም ይላሉ። ይህ አይነቱ ባህሪ ከእውነተኛ ሙስሊም ባህሪ የራቀ ነው። እውነተኛ አማኞች ከአሏህና ከመልዕክተኛው የተገለፀውን ማንኛውንም ነገር እውነት ነው ብለው ይቀበላሉ።

## እጅ መስጠት:እራስን ማስገዛት

አራተኛው የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታ እጅ መስጠት ወይም ኢንቂያድ ሲሆን ይህ ሸሃዳን በተግባር በስራዎቻችን መግለፅ ነው። በእርግጥ ይህ በራሱ ኢስላም

ከሚለው ቃል ትርጉሞች ውስጥ አንዱ ሲሆን ለአሏህ ፍቃድና ትዕዛዝ እራስን ማስገዛት ማለት ነው። አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ሲል ያዘናል፡-

**=<({አል-ቁርአን 39:54})>=**

وَأَنِيبُوٓاْ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ وَأَسۡلِمُواْ لَهُ

**{54} *ወደ ጌታችሁ በተውበት ተመልሱ፤ ለእሱም ታዘዙ!***

እነዚያ ለትዕዛዙ በተግባር እራሳቸውን ያስገዙትን አሏህ እንዲህ ሲል አወድሷቸዋል፡-

**=<({አል-ቁርአን 4:125})>=**

وَمَنۡ أَحۡسَنُ دِينٗا مِّمَّنۡ أَسۡلَمَ وَجۡهَهُۥ لِلَّهِ وَهُوَ مُحۡسِنٞ

**{125} *ፊቱን ለአሏህ ከሰጠ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱን ያሳመረ ማን ነው።***

በእርግጥ አሏህ ለእሱ እና ለመልዕክተኛው ትዕዛዝ እጅ መስጠትን ወይም እራሳን ማስገዛትን የኢማን ቅድመ ሁኔታ አድርጎታል። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 4:65})>=**

فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤۡمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيۡنَهُمۡ ثُمَّ لَا يَجِدُواْ فِ
ىٓ أَنفُسِهِمۡ حَرَجٗا مِّمَّا قَضَيۡتَ وَيُسَلِّمُواْ تَسۡلِيمٗا

**{65} በጌታህ እምላለሁ! በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስካላስፈረዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከሚያገኙና በፍፁም መታዘዝን እስኪታዘዙ ድረስ አማኞች አይሆኑም።**

በእርግጥም ሸሃዳችነን ወይም የእምነት ምስክርነታችን በልባችን ፣ በምላሳችን እና  በተግባራችን ሊፈፀም ይገባል። በልባችን የአሏህ ፍቅር ፣ የአሏህ ፍራቻና በእሱ ላይ ተስፋ ማድረግ ሊኖረን የሚገባ ሲሆን በምላሳችን ሸሃዳን ከመሰከርን ሸሃዳ ከኛ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ደግሞ በተግባር መፈፀም ይኖርብናል። ለምሳሌ ሶላት መስገድ ፣ መፆም ፣ በመፀሐፎቹና በመልዕክተኞቹ ማመን ፣ የአምልኮት ተግባራትን በሙሉ ለአሏህ ብሎ ማድረግን ያጠቃልላል።

ምንም አይነት ስራዎችን  ሳይሰራ እኔ ሙስሊም ነኝ የሚል ሰው አንድም ኢስላምን አልተረዳም ወይም ደግሞ በራሱ ላይ የመሰከረው የእምነት ምስክርነት ሸሃዳ ከልቡ አይደለም ማለት ነው። ይህ ማለት ሙእሚን የሆነ ሰው ሃጢያት አይፈፅምም ማለት አይደለም። በእርግጥ አማኝ ሁኖ ሃጢያት ሊፈፅም ይችላል። ነገርግን የሚሰራው ነገር ትክክል አለመሆኑን ሲረዳ በተውበት ቶሎ ብሎ ይመለሳል።

# እውነተኛነት

አምስተኛው ቅድመ ሁኔታ እውነተኝነት ሲሆን ይህ የውሸት ተፃራሪ ነው። ይህ ማለት ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የአሏህ መልዕክተኛና ባሪያ መሆናቸውን ስንመሰክር እውነተኛዎች ሁነው ወይም ከልባችን ሁኖ መሆን አለበት።

በቡኻሪ እና ሙስሊም እንደተዘገበው

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን ከልቡ በቅንነት የሚመሰክር የለም አሏህ የጀሃነምን እሳት ለእሱ እርም ያደረገለት ቢሆን እንጅ ብለዋል።

ሆኖም አንዳንዴ ይችን የምስክርነት ቃል ከልባቸው ሳይሆን ከላዩ ላይ ጥቅም አይተውበት እንዲሁ ከልባቸው ሳይሆን ከላይ የሚመሰክሩ ሰዎች አሉ። ሆኖም ይህ አይነቱ ምስክርነት ምንም የማይጠቅም ምስክርነት ነው። ይህን የሚያደርጉት እራሳቸውን ለመጠበቅ ወይም ጥቅም ለማግኘት ብለው ቃሉን ይናገራሉ። ሆኖም እነዚህ አይነት ሰዎች ሙናፊቆች ናቸው። አሏህ እንደዚህ አይነት ሰዎችን እንዲህ ሲል ገልፃቸዋል።

**=<({አል-ቁርአን 2:8-10})>=**

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَبِٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَمَا هُم بِمُؤۡمِنِينَ
( ٨ )

يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَمَا يَخۡدَعُونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمۡ وَمَا يَشۡعُرُونَ
( ٩ ) فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٞ فَزَادَهُمُ ٱللَّهُ مَرَضٗاۖ وَلَهُمۡ عَ
ذَابٌ أَلِيمُۢ بِمَا كَانُواْ يَكۡذِبُونَ ( ١٠ )

**{8} ከሰዎችም ሳያምኑ በአሏህና በመጨረሻው ቀን አምነናል የሚሉ (ሙናፊቆች) አሉ።**

**{9} እራሳቸውን ብቻ የሚያታልሉ ሆነው እያለ እማያውቁ ሆነው አሏህን እና እነዚያ ያመኑትንም ያታልላሉ።**

**{10} በልቦቻቸው ውስጥ (የጥርጣሬና የንፍቅና) በሽታ አለ። አሏህም በሽታቸውን ጨመረባቸው። ይዋሹት በነበሩት ምክኒያት አሳማሚ ቅጣት አላቸው።**

በኢስላም አምነው ሳይሆን ሙስሊም በመሆናቸው ጥቅም እንደሚያገኙበት አስበው ሙስሊም ነን የሚሉ በእለተ ትንሳኤ ሸሃዳቸው ተቀባይነት የማይኖረው ሲሆን በመዋሸታቸውም አሳማሚ ቅጣት ይገጥማቸዋል። ይሁን እንጅ በክህደት ላይ የነበረ ሰው ኢስላምን ሲቀበል እሱ አምኖበት ሳይሆን ዋሽቶ ነው ወይም ጥቅምን ፈልጎበት ነው ማለት አንችልም። የውስጥን አዋቂ አሏህ ብቻ ነውና።

## ኢህላስ: ቅንነት

ስድስተኛው የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታ ቅንነት ወይም ኢህላስ ሲሆን የሽርክ ወይም በአሏህ ላይ ባላንጣ የማበጀት ተቃራኒ ወይም ተፃራሪ ነው። ሆኖም ሸሃዳ በምናደርግ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ለአሏህ ብለን መሆን አለበት እንጅ በሌላ ምክኒያት ለማንም ለምንም ነገር ብለን ማድረግ አይኖርብንም። አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 39:2})>=**

**فَٱعۡبُدِ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ**

***{2} ሃይማኖትን ለእሱ ብቻ ያጠራህ ሆነህ አሏህን ተገዛው።***

**=<({አል-ቁርአን 98:5})>=**

**وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلۡقَيِّمَةِ**

***{5} ሃይማኖትን ለእሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው አሏህን እንዲገዙት ፣ ሶላትን እንዲሰግዱ ፣ ዘካንም እንዲሰጡ እንጅ አልታዘዙም። እናም ያ ቀጥተኛው ሃይማኖት ነው።***

በሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) የአሏህን ፊት(ውዴታ) ፈልጎበት ከአሏህ ውጭ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ የለም ያለ ሰው አሏህ የጀሃነምን እሳት ከእሱ እርም አደረጋት ብለዋል።

ይህ ሁላችነም ልናስብበት የሚገባ ነገር ነው። በተለይ በሙስሊም ቤተሰብ ውስጥ ሁነን ያደግን ሰዎች። ሙስሊም የሆነው ለአሏህ ብቻ ብለን እንጅ ለቤተሰቦቻችን ፣ ለጎደኞቻችን ፣ ለማህበረሰቡ ብለን እንዳልሆነ ለራሳችን ግልፅ ልናደርገውና ነፍሶቻችንንም ልንመረምርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ሙስሊም የሆነው ለአሏህ ብለን መሆኑን ከሚያመላክቱ ነገሮች አንዱ አሏህና መልዕክተኛው ያዘዙትን ማንኛውንም ነገር መስራታችን ነው። ነገርግን አሏህና መልዕክተኛው ያዘዙንን ነገሮች ሰዎች አዩኝ አላዩኝ እያልን የምሰራ ከሆነ ወይም ሰዎች ሲያዩን መልካም ስራዎችን የምንሰራ ፣ ሳያዩን የምንተው ከሆነ ግን ስራዎቹን የምንሰራው ለሰዎች ብለን እንጅ ለአሏህ ብለን እንዳልሆነ ያመለክታል። ስለዚህ ሁሉንም ስራዎቻችነን ስንሰራ ሙሉ በሙሉ ለአሏህ ብለን መሆን አለበት።

እንዲሁ አንዳንዴ በሸሪአው የተደነገጉ ነገሮችን ከመመልከት ይልቅ እነንትና እነንትና እየሰሩት አይደል እንላለን። አንዳንዴም ቤተሰቦቻችነን ወይም ጎደኞቻችነን ለማስደሰት ብለን በሸሪአው የተደነገጉትን ነገሮች ወደጎን ትተን እነሱ የሚደስቱበትን ወይም ፋራ የማያስብለንን ነገር እንፈፅማለን። ለምሳሌ ከሰዎች ጋር ተግባቢ ነው ከምንባልበት ሴቶች ከወንዶች ጋር ወንዶች ከሴቶች ጋር መቀላቀልና መጨባበጥ እንዲሁም ከቤተሰቦቻችን

ትችት ለመራቅ ስንል ከማናውቃቸው ሴቶች ጋር እንቀላቀላለን እንጨባበጣለን። ይህኔ ሁላችነም ለምን ሙስሊም እንደሆን በቅንነት እራሳችነን ልንጠይቅ ይገባል። እውነት ሙስሊም የሆነው ለአሏህ ብለን ነው ወይስ ለቤተሰቦቻችን እና ለጎደኞቻችን?

## ውዴታ

ሰባተኛው ቅድመ ሁኔታ ውዴታ ሲሆን ሸሃዳን እና የያዘችውን ነገር መውደድ እንዲሁም ለሸሃዳ ሲሉ የሚሰሩትን እና የሚጥሩትንም ሰዎች መውደድ ጭምር ነው። ሸሃዳ አድርገን ነገርግን በእሷ ላይ ውዴታ ከሌለን በእርግጥ እምነታችን ሙሉ አይደለም። ይህ የእውነኛ አማኞች ባህሪም አይደለም። ከሸሃዳ ወይም ከአሏህ በላይ ሌላ ነገርን ከወደድን ሸሃዳችነን አፍርሰናል። ምክኒያቱም እውነተኛ አማኞች የምንሆነው በሸሃዳ ላይ ውዴታ ሲኖረንና በውዴታችነም የተነሳ ከአሏህ ጋር አንድ አቻ ወይም ባላንጣ ባለደረግን ጊዜ ነው። አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 2:165})>=**

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَاد ً ا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ ٱللَّهِ ۖ
وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَشَدُّ حُبً ّ ً ا لِّلَّه

**{165} ከሰዎችም ከአሏህ ጋር ባላንጣን አድርገው የሚይዙ አሉ። አሏህን እንደሚወዱትም ይወዷቸዋል። ነገርግን እነዚያ አማኞች አሏህን በጣም ይወዱታል።**

በቡኻሪና ሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ሶስት ባህሪያቶች ያሉት ሰው የኢማን ጥፍጥና አለው ካሉት መካከል አንዱ አሏህንና መልዕክተኛውን ከማንኛውም ነገር አብልጦ የሚወድ የሆነ ሰው ነው።

## በጣኦታቶች መካድ

ስምንተኛው የሸሃዳ ቅድመ ሁኔታ ከአሏህ ውጭ የሚመለኩ ጣኦቶችን ውድቅ ማድረግና አለመቀበል ነው። በእርግጥ ይህ ቅድመ ሁኔታ በሸሃዳ መርህ ውስጥ የሚገኛ ቢሆንም የበለጠ አፅንኦት ለመስጠት ተገልፃል። ሸሃዳ ማረጋገጥን ብቻ ሳይሆን ውድቅ የማድረግን መርህ አቅፋ ይዛለች።

**=<({አል-ቁርአን 2:256})>=**

**فَمَن يَكْفُرْ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسْتَمْسَكَ بِٱلْعُرْوَةِ ٱلْوُثْقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَا ۗ**

**{256} በጣኦት የሚክድና በአሏህ የሚያምን ሰው በእርግጥ የማትበጠስን ጠንካራ ዘለበት ጨበጠ!**

## ማጠቃለያ

ውድ ሙስሊም እህት ወንድሞቼ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የተፃፉት ለትምህርት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዳችን እራሳችነን እንድንፈትሽና እንድንመረምንር ጭምር ነው። ሸሃዳየ እነዚህን አስፈላጊ ነገሮች አሟልቷል? እውነት በኢህላስ ፣ በእውነተኝነትና አሏህን በመውድ ነው ያልኩት? እውነት ይህ የምስክርነት ቃል ምን ማለት እንደሆነ ተረድቸው ነው ያልኩት? እውነት ከአሏህ ውጭ የሚመልኩ ነገሮችን ሁሉ ውድቅ አድርጌያለሁ? የአምልኮት ተግባራቶችንስ በሙሉ ለአሏህ ብቻ እድርጌያለሁ?

እነዚህን ጥያቄዎች እራሳችነን በመጠየቅ ውስጣችን ላይ ያለውን መልስ እንመልከት። መልሶቻችን በሙሉ ትክክል ከሆኑ አልሃምዱ ሊላህ ነገርግን መልሶቻችን ላይ እንከኖች ካሉ ዛሬውኑ እንከኖቻችነን አስወግደን ሸሃዳችነን ሙሉ ማድረግ አለብን። ኢንሻ አሏህ አሏህ ፍቃዱ ከሆነም ሸሃዳችን የጀነት ቁልፍ ይሆንልናል፤ በዛች የሰላም ምድር ጀነት ለዘላለም እንኖራለን።

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!